282261
የፍ/ብ/መ/ቁ.265597
ቀን 27-07-2014 ዓ.ም

ዳኛ፡- ፍሬህይወት ተሾመ

ዳዊት በላይ

እንዳለ ታደሰ

ከሳሽ፡- የኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር-ጠ/ከድር ቡሎ ቀረቡ

ተከሳሽ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ-ተወካይ ወንጌል አባተ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጧል።

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው ከሻስ በ19/06/13 በተጻፈ የክስ መመስረቻ ጽሁፍ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 261658 በ10/07/2013 በሰጠው ውሳኔ የከሳሽን መከራከርያ ማስረጃ በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥ በተወሰነው መሰረት ተከሳሽ በ28/03/2013 የሰጠውና ለከሳሽ በ02/04/16 ከሳሽን ከተወዳዳሪ ፓርቲነት በመሰረዝ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ በማቅረቡ ነው። የአቤቱታው ዋና ዋና ነጥቦችም የሚከተሉት ናቸው።

### 1) የመከላከል መብትን በተመለከተ

ማንኛውም አስተዳደራዊ ውሳኔ ሲሰጥ የሚመለከተው አካል የቀረበበትን ክስ የማወቅ፣ ራስን የመከላከል፣ በገለልተኛ ዳኛ የመዳኘት እና የመሰማት መብት የተጠበቀለት መሆኑ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት እውቅና ተሰጥቶታል። ሆኖም ተከሳሽ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት መከራከርያ እንድናቀርብ የወቅቱን የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በቂ ጊዜና ዕድል መስጠት እያለበት ከሳሽ ሐምሌ 20 2013 ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ ነሐሴ 10 2013 በተጻፈ ደብዳቤ ከ21 ቀናት ባነሰ ጊዜ እስከ ጳጉሜ 1 2013 እንዲቀርብ በማለት ማሳወቁን ይህ ጊዜ አስከፊ የጸጥታ ችግር ባለበት ይቅርና በሰላሙም ጊዜ የትራንስፖርት ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች ስለሚጨምር አሟልቶ ማቅረቡ አይሞከርም። ይህን የተጨማሪ ጊዜ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ፈጽሚያለሁ ለማለት ያህል ውድቅ በማድረግ በህግ የተጠበቀልንን አስፈላጊ ማስረጃ በማቅረብ የመከላከል መብት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ

98 (3) አስገዳጅ ድንጋጌ እና በሀገ መንግስታችን እውቅና የተሰጠውን መሰረታዊ የተፈጥሮ ፍትህ መርሆችን የጣሰ ስለሆነ የህግ መሰረት የለውም።

## 2) የግልጸኝነትን መርህንና ህግን ያላገናዘበ ውሳኔ መሆኑን በተመለከተ

የቦርዱ ግልጽ አሰራር የሚለካው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ባለድርሻዎችን ማሳተፉ ላይ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ 108 አባላት መዋሪነትን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ተጣቶ በወረዳቸው ወይም ቀበሌያቸው ነዋሪ አለመሆናቸው እንደምክንያት ተጠቅሷል። ሆኖም ማጣራቱ የተደረገው ክሳሽ በሌለበት ግልጸኝነት በሌለው፣ አሳታፊ ባልሆነናየሃገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ባለገናዘበ ነው። ተከሳሽ ናሙናውን እንዴት እንደወሰደ፣ ናሙና ማረጋገጫ ቦታዎችን በምን መመዘኛ እንደመረጠ፣ ምን ዓይነት የማጣርያ መንገድ እንደተጠቀመና ይህን ሲያከናውን ባለድርሻ አካላትን የማሳወቅ እና ማሳተፍ ግዴታውን ስለመወጣቱ የገለጸው ነገር የለም። ክሳሽ ተከሳሽ የሰበሰበውን መረጃ እና ሪፖርት፣ የክልል ምርጫ ቦርድ የሰጠውን አስተያየትና የደብዳቤ ልውውጦች፣ የውሳኔውን ቃለ ጉባኤ ግልባጭ እና አሰራሩን ግልጽ እንዲያደርግ ተከሳሽን በደብዳቤ ቢጠይቅም ፍቃደኛ አልሆነም። ይህም ተከሳሽ የተከተለው ግልጸኝነት የጎደለው አሰራር መሆኑን ያስረዳል።

ቦርዱ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ባለድርሻ አካላት ሳያሳውቅ፣ በቦታው ባልተገኙበት ሁኔታ በብቸኝነት ከቀበሌ፣ ከወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ቀረበ ያለውን ማስረጃ ነው። ይሁን እንጂ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል በተለይም በገጠሩ አካባቢ መታወቂያ አውጥቶ የመኖር ባህል የለም። ቀበሌዎች የተሟላ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ማህደር የላቸውም። በፍርድ ቤት ተጨማሪ ማጣርያ ማድረግም የተለመደ ነው። ይህ ሁሉ በሆነበት ተከሳሽ ተጨማሪ ዘዴ በመጠቀም የማረጋገጥ ግዴታውን ሳይወጣ የገዢው ፓርቲና ህዝብ አስተዳደር ተቀላቅለው ባሉበት በስልጣን ላይ ላለው ፓርቲ ከሆኑ ከታችኛው የመንግስት አካል የተሰጠውን ተዓማኒነት የሌለው ማስረጃ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የህግም ሆነ የማስረጃ ድጋፍ የለውም።

ተከሳሽ ራሱ በ13/04/13 በሰጠው መግለጫ መረጃውን ሰብስበዋል የተባሉት አካላት የተሟላ መረጃ ባለመያዛቸው እክል እንደገጠመው አምኖ ባለበት ይህን መንገድ ተከትሎ በተገኘ ማስረጃ ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊነት የለውም።

## 3) አስፈላጊውን መረጃ በጥንቃቄና በበቂ ሁኔታ የማሰባሰብ ግዴታ ያልተወጣ ስለመሆኑ

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 98(3) ላይ የፓርቲ መሰረዝ ውሳኔ ቦርዱ ከመስጠቱ በፊት የሚመለከተው የፖለቲካ ፓርቲ መከላከያውን አቅርቦ እንዲያሰማ የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ቦርዱ ግን ክሳሽ አስተያየት እንዲሰጥ ሳያደርግ፣ ማብራሪያና ተቃራኒ ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ሳይሰጠዉ የምርጫ ህጉን እና የፓርቲዉን መስራች አባለት ህገ መንግስታዊ የመደራጀት መብትን በተጻረረ መልኩ አስተማማኝ ባልሆነና ተቃራኒ ፍላጎት/conflict of intrest/ ካለዉ ወገንተኝነቱ ስልጣን ላይ ላለዉ ፓርቲ ከሆነዉ ከበታች አስተዳደር አካል በተሰበሰበ ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ የተሰጠዉ የመሰረዝ ዉሳኔ የህግ መሰረት የሌለዉ ነው፡፡

አሁን ባለዉ ተጨባጭ መረጃ መሰረት ከሳሽ በሚወዳደርበት በምእራብ ኦሮሚያ አካባቢ ረጅም ጊዜ 3 ሳምንት ወስደዉ አጣርተው ባገኙት ዉጤትም ከ80-90 በመቶ የመሰራች አባላት መሆናቸዉን ተረጋግጦ እያለ በምስራቁ ባግባቡ ማጣራት ባለመደረጉ ህብረተሰቡን ያለ ተወካይ የፖለቲካ ፓርቲ በሚያስቀር መልኩ እንዲሰረዝ መደረጉ በአንድ በኩል ቦርዱ እኛ እንወክለዋለን የምንለዉን ህብረተሰብ በህግ ከተጠበቀለት በፖለቲካ የመሳተፍ መብት ዉጭ ማድረግ የፖለቲካ ድርጊት በመሆኑ ቦርዱ የሰጠዉ ዉሳኔ ፍትህን፣ የህዝቦችን መብት እና የእኩልነት መርህን የሚጻረር ነው፡፡

**4) ቦርዱ የመስራች አባላት ናሙና ሲጣራ ከ35 በመቶ በታች ነዋሪ አለመሆናቸዉ ከተረጋገጠ የህጉን መሰፈርት እንዳላሟሉ ተድረጎ እንዲቆጠር መወሰኑን በተመለከተ**

አንድ ፓርቲ አስፈላጊዉን መመዘኛ ማሟላት አለማሟላትን በተመለከተ ልዩነት መፍጠሪያ ነጥብ(cut point) በመቶኛ ለማስቀመጥ ፈቃጅ ሊኖር ይገባል፡፡ በአዋጅ 1162/2011 ላይ ግን ቦርዱ ይህን ስልጣን የሚሰጠዉ ድንጋጌ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ቦርዱ ያለ ምንም የህግ መነሻ ለዚያዉም ጉዳዩና በምርጫ የሚሳተፉበት የኦሮሚያ ምርጫ ቦርድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለቦርዱ በላከዉ ሪፖርት ከቀበሌዎች በተገኘዉ መረጃ ብቻዉን ዉሳኔ ለመስጠት በቂ ባለመሆኑ ሌላ የመረጃ ማገናዘቢያ መንገድ እንዲቀረጽ  ምክረሀሳብ በመስጠት ጭምር ገልጾ እያለ ያለምንም መመዘኛ በህግ ዉስጥ የሌለ መቶኛ ስሌት በማስቀመጥ የዜጎችን የመደራጀት መብት በሚገድብ መልኩ ከፖለቲካ ፓርቲነት የሚሰርዝ ዉሳኔ ማስተላለፉ ህግን ያልተከተለ ነው፡፡

**5) የቦርዱ ውሳኔ የማጣራት ሂደቱ አስተማማኝ አለመሆኑና ለውሳኔ በቂ ያልሆነ መረጃ መሆኑን የሚገልጽ ምክረ ሃሳብን ያላገናዘብ መሆኑን በተመለከተ**

አመልካች በሚወዳደርበት የኦሮሚያ ምርጫ ቦርድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለቦርዱ ከቀበሌዎች ከወረዳዎች ተላከው ማስረጃ በቂ አለመሆናቸውን የመረጃ ማገናዘቢያ እንዲቀረጽ ምክረ ሃሳብ ሰጥቷል፡፡ ይህ በሆነበት ምክረ ሃሳቡን ችላ በማለት የተሰጠዉ ዉሳኔ ሊሻር ይገባል፡፡

6) የተከሳሽ ውሳኔ የተጠሪነት መርህን የጣሰ ስለመሆኑ

ከሳሽ ማጣራቱ ተዓማኒነት እንዲኖረው ከሳሽን ባሳተፈ መልኩ መሆን አለበት የሚል ቢሆንም ተጠሪ ጥያቄው ውድቅ በማድረግ ከአንድ ተጻራሪ ፍላጎት ካለው ወገን የቀረበ ሪፖርት ላይ በመመስረት የተሰጠው የመሰረዝ ውሳኔ የገለልተኛነት መርህን መሰረት ያላደረገ እንደሆነ ያሳያል፡፡

እንዲሁም ተከሳሽ አባላቶቻችንን ቦርዱ ጋር ከሚገኘው የመራጮች መዝገብ እንዲያጣራ ስንጠይቅ ከመራጮች መዝገብ ማጣራት የሚቻልበት ህጋዊ መሰረት የለም የመራጮች መዝገብም የሚያረጋግጠው ለ6ኛ ሃገራዊ ምርጫ መመዝገብን ብቻ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የማጣራት ሂደቱ ዓላማው እውነትን ለማረጋገጥ መሆኑ እየታወቀ ይህን የሚያዝ ህግ የለም ብሎ ማስረጃው እንዳይቀርብ መከልከሉ ህግን ያልተከተለ ነው፡፡

ተከሳሽ እንደ አንድ ዲሞክራሲያዊ ተቋም ለፓርቲዎች አስቻይ ሁኔታዎችን እየፈጠረ የዜጎች ተደራጅቶ የመሳተፍ መብትና በገለልተኛነት የበለጠ ማስከበር ግዴታ እያለበት የዜጎችን የፖለቲካ ተሳትፎ የመገደብ አንደምታ ያለው ውሳኔ መስጠቱ አግባብ ስላልሆነ ህገ መንግስታዊ መብትን በሚያከብር መንገድ ውሳኔውን እንዲያስተካክል እንዲደረግና ውሳኔው እንዲሻር እንጠይቃለን የሚሉ ናቸው፡፡

ይህ አቤቱታ ለተከሳሽ ከፍርድ ቤቱ መጥርያ ጋር ተልኮለት በ19/05/14 በሰጠው መልስ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 261658 የሰጠው ፍርድ የተከራካሪ ወገን የመሰማት መብት ተከብሮ ውሳኔ አልተሰጠም የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ከሳሽ በዚህ መዝገብ ሊያቀርብ የሚገባው የይግባኝ ምክንያት የመሰማት መብት ሳይከበር ውሳኔ ተሰጥቷል የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማስፈጸም ካለው አስተዳደራዊ ኃላፊነት በመነሳት ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከደረሰው ጀምሮ ከከሳሽ ጋር በመነጋገርና በመስማማት 6 ወራት ከቆየ በኃላ መከላከያውን እንዲያቀርብ ጠይቋል፡፡ በዚህ ጊዜ ባለማቅረቡ በድጋሚ ነሐሴ 10 2013 እንዲያቀርብ አሳውቀናል፡፡ ይህም ውሳኔ ከተሰጠበት ጀምሮ ለ6 ወራት ሲዘጋጅ እንደቆየ ነው፡፡ ይህ በሆነበት ጊዜ አነሰ ማለቱ ከሳሽ ቸልተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከሳሽ ሐምሌ 2013 በተጻፈ ደብዳቤ ነዋሪ አለመሆናቸው የተረጋገጠላቸው 108 ሰዎች ስም ዝርዝር እንዲሰጠው ጠይቆ ዝርዝር ተሰጥቶት እስከ ጳጉሜ 5 2013

መከላከያ አቅርብ ሲባል አንድ ዓመት እንዲሰጠው እና አባላቶቹ ለ6ኛ ጠቅላላ ምርጫ የተመዘገቡ ስለሆነ ከመራጮች መዝገብ እንዲጣራ ውስን ሰዎች በህይወት እንደሌሉ እና ወጣቶች ሃገራዊ ጥሪ በመቀበል ወራዊት መቀላለቀላቸውን ገልጿል፡፡ ከሳሽ ትክክለኛ ማስረጃ ማቅረብ እያለበት ከመራጮች መዝገብ አጣሩ ማለቱ የመሰማት መብቱን ተግባራዊ ማድረግ እንዳልፈለገ ያሳያል፡፡ ተከሳሽ ከመራጮች መዝገብ የሚያጣራበት ምክንያት የለም፡፡ ከሳሽ ተሰጠኝ ባለው 25 ቀናት ውስጥ ምን እንደሰራ አላስረዳም፡፡ ተከሳሽ ማጣራቱን ያደረገው አካባቢውን ከሚያስተዳድረው አካል ጋር መሆኑ የህግና ማስረጃ ድጋፍ አለው፡፡ ተከሳሽ ናሙና በመውሰድ ማጣራቱ ቀድሞ በተደረገው ክርክር የታመነበትና የታለፈ ጉዳይ ስለሆነ አቡን ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ በቀደመው ፍርድ ላይም በተጨማሪ ማስረጃ እንዲጣራ የተወሰነ የለም፡፡ ቦርዱ በሚመቸው መንገድ የማጣራት ስልጣን አለው፡፡ ቦርዱ ገለልተኝነት መርህን ያልተከተለ ለሚለው ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለዚህ ውሳኔው ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በማስረጃነትም መከላከያውን እንዲያቀርብ ጻፍኩት የሚለው ደብዳቤ፣ ፓርቲው ምላሽ የሰጠባቸው ደብዳቤዎች፣ ስም ዝርዝር የያዘ ሰነድ እና ውሳኔ ተያይዘዋል፡፡

በክስ መስማት ወቅትም ከሳሽ መከላከል እንድንችል ጊዜ ተሰጥቶናል ነገር ግን በቂ አይደለም፣ ጦርነት ስለነበር ጊዜ ሊሰጠን ይገባ ነበር፣ ከመራጮች ዝርዝር እንዲጣራ ጠይቀን ፍቃደኛ አልነበረም፣ የተሰጠው ጊዜ ከተቋሙ ኃላፊነት ጋርም አይሄድም፣ ማጣራት መደረግ ያለበት ባለንበት ነበር፣ ጊዜ ይሰጠንና ማጣሪያውን እናደርጋለን፣ ከ108 አባላት የቱም ላይ ማጣርያ አላደረግንም፣ ጥያቄያችን ከጊዜ አንጻር ነው ነባራዊ ሁኔታ ግን ግምት ውስጥ ይግባልን ነው የምንለው፣ በመጀመርያ የሰበሰብነው መታወቂያ አልነበረንም ያለ ሲሆን ተከሳሽ በበኩሉ ቀድሞ የነበረው ክርክር ዕልባት አግኝቷል፣ በህጉ በተቀመጠው መሰረት ጊዜ ሰጥተን መስማት መብቱን ጠብቀናል፣ የተሰጣቸውን ሊጠቀሙ አልቻሉም ምን ያህል ጊዜ እንደሚሉም አላስቀምጡም ብሏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ይህን ሲመስል ይህ ፍርድ ቤትም 1) ተከሳሽ ከሰጠው ውሳኔ ጋር በተገናኘ ከሳሽ የመሰማት እና ራሱን የመከላከል መብቱ እንዳልተጠበቀለት ገልጾ ያቀረበው ክርክር አግባብ ነው አይደለም 2) ተከሳሽ ከሳሽን ከፓርቲነት በመሰረዝ የሰጠው ውሳኔ የግልጽነት መርህን የተከተለ ነው አይደለም 3) ተከሳሽ ከሳሽ ፓርቲን ከአባልነት መሰረዙ አግባብነት ያለው ነው አይደለም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምሯል፡፡

የመጀመርያውን ጭብጥ በተመለከተ

ከሳሽ የመደመጥና የመሰማት መብት አልተጠበቀልኝም የሚለው ለማጣራት በቂ ጊዜ አልተሰጠም በሚል ነው፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት እንደተቻለው ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 261658 የተሰጠው ውሳኔ (በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መጋቢት 10 2013 እንደጸናው) መሰረት ጉዳዩ የተመለሰው የማጣራት ስራውን ተከትሎ የደረሰበትን ውጤት በሚመለከት ውሳኔ ከመስጠት በፊት ለአመልካች ያሳወቀበት መንገድ የለም አባላቱ ያልተገኙበትን ምክንያት ማብራርያ እንዲሰጥና ራሱን እንዲከላከል አልፈቀደም በሚል ነው፡፡

ከክርክሩ እንደሚታየው ቦርዱ 6 ወራት ለከሳሽ ሰጥቶ የነበረ ለመሆኑ ተከሳሽ ያቀረበውን ክርክር ከሳሽ አልካደም፡፡ ከዚህ ጊዜ በኃላም ከሳሽ ሐምሌ 7 2013 ውጤቱን ሲገልጽ ከሳሽ ተጨማሪ ጊዜ ጠይቆም ተከሳሽ እስከ ነሐሴ 10 2013 ውጤቱን እንዲገልጽ ጊዜ መስጠቱ ላይ ሙተማመናቸው ይታያል፡፡ ይህ ከሆነ በኃላ በቂ ጊዜ አልተሰጠም ሚል የቀረበው ክርክር አግባብነት ያለው አይሆንም፡፡

የከሳሽ ዋና ክርክር አባላቶቹ ያሉበት አካባቢ ባለው ጸጥታ ችግር ምክንያት ማስረጃዎችን ለማቅረብ ስለሚቸገር የተሰጠው ጊዜ አጭር ነው የሚል ነው፡፡ ከዚህም ከሳሽ ውሳኔው እንዲሻርለት የጸጥታ ችግርን እንደዋነኛ ምክንያት ባይጠቅስም ለክርክሩ ማጠናከርያነት እንዳቀረበው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ይጣሩ የተባሉት መስራች አባላት ነዋሪነታቸው ወይም የሚገኙት በእነዚህ የጸጥታ ችግር አለባቸው የተባሉ አካባቢዎች ለመሆኑ ከሳሽ ያቀረበው ክርክር ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ እንዲሁም ይህ የጸጥታ ችግር ከሳሽ ላይ ብቻ ያጋጠመ አይደለም፡፡ ስለዚህ የተለየ እክል ከሳሽ እንደተፈጠረበት ሊወሰድ የሚችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡

በተጨማሪም ከሳሽ የመጀመርያው የተከሳሽ ውሳኔ ከተሻረ በኃላ በነበረው ጊዜ አባላት አድራሻ እና ሁኔታዎች ማሟላት የሚችልበት ዕድል እያለው ይህን ሳያደርግ ቀርቷል፡፡

ሌላው ከሳሽ የሚያነሳው አባላቶቹ መንግስት ባደረገው ጥሪ መሰረት በመከላከያ ሰራዊት አባልነት ተቀላቅለዋል የሚል ነው፡፡ ሆኖም በፍርድ ቤቱ እምነት የከሳሽ አባላት ሰራዊቱን መቀላቀላቸው ነዋሪነታቸውን ከአድራሻቸው ማጣራት ስራ የሚከለክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የማጣራት ስራው በወቅቱ በአካባቢው መኖራቸውን የሚመለከት ሳይሆን ቀድሞ የነበረው አድራሻ ነዋሪ መሆናቸው ብቻ መሆኑ ነውና፡፡ ይህም በአስተዳደር ካሉ ማስረጃዎች የሚገኘውን እንጂ በአካል መገኘትን የግድ የሚል አይደለም፡፡

ከሳሽ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ለማሟላት ያህል ጊዜ ሰጠሁ ለማለት እንጂ በቂ ጊዜ አልተሰጠም በማለት መከራከሩ ቢ.ታይም ከሳሽ የሰጠው ጊዜ ከቅን ልቦና ውጪ ተከሳሽ ያደረገውና ትዕዛዙን አክብሬያለሁ ለማለት ብቻ ያከናወነው ለማለት የሚያበቃ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ስላላገኘ ክርክሩን አልተቀበለውም።

በመሆኑም አሁን በሃገሪቱ ያለው ሁኔታ ሲገናዘብ የተሰጠን ጊዜ አጭር ነው በማለት ነው ከሳሽ ያቀረበው ምክንያት አሳማኝነት የሌለውና በቂ ጊዜ አልተሰጠውም ለማለት የሚያበቃ ሆኖ አልተገኘም።

ከሳሽ የመከላከል መብቴ አልተከበረልኝም የሚለውን ክርክር እንደሚያሳይለት አድርጎ የሚያቀርበው ሌላኛው ነጥብ ተከሳሽ የመስራች አባላትን ማጣራት ሲያደርግ አላሳወቀኝም የሚል ነው።

የመስራች አባላትን መረጃ ትክክለኛነት ቦርድ የሚያጣራበት አግባብ የተቀመጠው በአዋጁ አንቀጽ 65(3) እና ይህ ድንጋጌ በሚመራው አንቀጽ 64(4) እና (5) መሰረት ነው።

በዚህ አንቀጽ 64 (5) ድንጋጌ ላይ የተቀመጠው ደግሞ የመስራች አባላት መረጃ በተጭበረበረ መንገድ የቀረበ እንደሆነ ቦርዱ በራሱ ሊያጣራ እንደሚችል ነው። ይህንንም በድንጋጌው ላይ "... ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት..." በሚል ከተቀመጠው ሐረግ መገንዘብ ይቻላል።

እንዲሁም ከሳሽ መስራች አባላቶቼ የሚላቸውን ሰዎች ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ አሟልቶ በቃለ መሐላ አረጋግጦ ለቦርዱ እንደሚያቀርብ ከድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል። በዚህ መልክ ያሳወቀው ወይም ያስገባው ማስረጃ በማንኛውም ሰዓት ማጣራት ሊደረግበት እንደሚችል ያውቃል ተብሎም ይታሰባል።

አንድ ፓርቲ ከዚህ መሰል መረጃ ጋር በተያያዘ የሚኖረው ዕድል መረጃውን ከማስገባቱ በፊት ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ብቻ ነው። አዋጁ ለተከሳሽ መረጃዎችን ለማጣራት ስልጣን የሰጠው ሲሆን በማጣራት ሂደት ውስጥ ፓርቲዎችን እንዲያሳትፍ በአስገዳጅነት የተቀመጠ ድንጋጌ የለም። ይህም የሚያሳየው የፓርቲዎች ተሳትፎ እንደመብት የሚጠየቅ ሳይሆን ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በሚያቀርበው ጥሪ ፓርቲዎች ሊሳተፉ የሚችሉበት መሆኑን ነው። አንድ ፓርቲ ራሱ አረጋግጦ የሰጠውን መረጃ ቦርዱ ለማጣራት በሚያደርገው ሂደት ውስጥ ሊሳተፍ የሚችለው እንደ መብት ሳይሆን ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ጥሪ ካደረገ ብቻ መሆኑንም መገንዘብ አያቅትም።

ከላይ በተቀመጠው የህግ ድንጋጌ መሰረት ተከሳሽ የማጣራት ኃላፊነቱ ሲሰጠው ፓርቲዎችን እንዲያሳትፍ በአስገዳጅነት ባልተቀመጠበት ሁኔታ ከሳሽ መረጃው ሲጣራ የመረጃው አግባብነትና ትክክለኛነት በሚመረመርበት ወቅት አልተሳፍኩም ብሎ ቅሬታ ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ የለም።

በምርጫ ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ፓርቲዎች የመከላከል መብት አድማስም የማጣራት ስራ ውጤት ከቀረበ በኃላ የተገኘ ውጤትን በተመለከተ አስተያየት መስጠት ከሚሆን በቀር ፓርቲዎች በተገኙበት እንዲጣራ መደረግ እንዳለበት የሚያስገድድ ሁኔታን አይጨምርም።

ከሳሽ ይህን የሚልበት ምክንያት ተከሳሽ መረጃ የጠየቃቸው አስተዳደር አካላት ለገዢው ፓርቲ ወገንተኝነት ያላቸው ናቸው በማለት ነው።

ተከሳሽ ይህን የማጣራት ስራ የሚያከናውነው መስራች አባላት ተብለው የተጠቀሱት ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ካሉ አስተዳደር አካላት ጋር በትብብር ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 65 እና 64 ላይ ተመልክቷል። ይህም በህግ የተመለከቱት የማጣራት ኃላፊነት ከተሰጣቸው ጋር ቦርዱ የሚያደርገው መሆኑን ያስገነዝባል። ይህም ለሁሉም ፓርቲ እኩል ተፈጻሚነት ባለው አዋጅ ላይ የተቀመጠ ነው።

ይህ በሆነበት በህግ ስልጣን የተሰጣቸውን አካላት ላይ ተከሳሽ ያለውን ስጋት መነሻ በማድረግ ማጣራት ሲደረግ እንዳውቅና እንድገኝ ልደረግ ይገባ ነበር በማለት የሚቀርብ ክርክር አሳማኝነት ያለው አይደለም።

ስለዚህ ከሳሽ በማጣራት ወቅት አለመሳተፉ ሆነ ማጣራት እየተከናወነ እንደሆነ እንዲያውቅ አለመደረጉ የመከላከል መብትን የሚጥስ ተግባር እንደሆነ የቀረበው ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ፍርድ ቤቱ ደምድሟል።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ

ከሳሽ ተከሳሽ የግልጽነት መርህን አልተከተለም በማለት ካነሳቸው ነጥቦች አንዱ ናሙና በመውሰድ ማጣራት ማድረጉ አግባብ አይደለም ይህን የሚፈቅድለት ህግ የለም የሚል ነው።

የመስራች አባላት መረጃን እና አሳሳች ማስረጃን በተመለከተ ቦርዱ የማጣራት ስልጣን እንዳሉት የሚያስቀምጡት የአዋጁ አንቀጽ 65 እና 64(4) እና (5) እና 98 ቦርዱ የማጣራት ስራውን የሚያከናውንበት ዘዴ ምን እንደሆነ አያመለክቱም። ይህም ቦርዱ አመቺ ነው የሚለውን መንገድ ለመወሰን የተተወለት እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው።

ይህ ፍቅድ ስልጣን የተተወለት ከሆነ ቦርዱ ናሙና በመውሰድ ማጣራት ዘዴን መከተሉ አግባብ አይደለም ሊባል የሚችልበት ምክንያት አይኖርም። ከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርም ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም።

በከሳሽ የተነሳው ሌላው የቅሬታ ነጥብ ተከሳሽ በናሙና ተወስደው ከተጣሩት 35% መስራች አባላት በታች ከሆነ እንዳላሟላ ይቆጠራል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መነሻ ህግ በሌለበት ነው የሚል ነው።

ይህ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የተነሳውን ክርክር እንደመረመረው ከላይ በተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የምርጫ ቦርድ የተሳሳተ የመስራች አባላት መረጃን በማጣራት ለሚወስደው እርምጃ መለኪያ ተብሎ በህግ አውጪው የተቀመጠለት የለም። መለኪያ በሌለበት ሁኔታ አጠራጣሪ ሆነ ማስረጃዎችን ለመለየት ከማስረጃዎቹ ምን ያክሉ የተሳሳተ ወይም ችግር ያለበት ሲሆን ምዝገባው ይሰረዛል ለሚለው ተከሳሽ መነሻ ማስቀመጡ የሚነቀፍ አይደለም።

አሁን የተያዘው ጉዳይ ከዚህ አንጻር ሲታይም ተከሳሽ ቦርድ ከመስራች አባላት መረጃ 108 ናሙናዎችን በመውሰድ አጣርቶ ከዚያ ውስጥ ከ35 በላይ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ከተገኘ መመዘኛው እንዳልተሟላ እንደሚወሰድ አስተዳደራዊ ውሳኔ መስጠቱን ገልጿል። ይህ ደግሞ በህጉ አስገዳጅ መነሻ በሌለበት ይልቁንም ከፍ ያለና ፓርቲዎችን የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርግ ለሁሉም ፓርቲዎች እኩል የሆነ አሰራር ተከሳሽ መዘርጋቱን ያሳያል። ይህን መመዘኛ ያሟላና ያላሟላ ተደርጎ መቀመጡም አግባብነት የለውም ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም።

ከሳሽ ከማጣራት ስራው ጋር በተያያዘ ያነሳው ሌላው ቅሬታ የመስራች አባላትን ማስረጃ ትክክለኛነት ለመወሰን ቦርዱ ከወረዳና ከቀበሌ የተገኘን ማስረጃ መሰረት ማድረጉ አግባብ አይደለም የሚል ነው።

በአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ (4) ላይ ቦርዱ ከመስራች አባላት መረጃ ጋር በተያያዘ አጠራጣሪ ነገር አጋጥሞ የማጣራት ስራውን ሲያከናውን አባላቱ በሚኖሩበት አካባቢ የነዋሪነት ማረጋገጫ የመስጠት ስልጣና ካለው አካል ጋር በመተባበር ሊያከናወን እንደሚችል ተመልክቷል። ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ቦርዱ የሚያስፈልገውን ማስረጃ ለማግኘት የሚጠቀመው በስራ ላይ ያሉ አስተዳደር አካላትን እንደሆነ ህጉ ማመላከቱን ነው። በመሆኑም ተከሳሽ ይህን በህጉ የተዘረጋውን መስመር ተከትሎ ማስረጃ እንዲቀርብ አደርጎ ማጣራቱ የሚነቀፍ አይሆንም።

ከሳሽ ይህን ተቃውሞ እያነሳ ያለው እነዚህ አስተዳደር አካላት ለገዢው ፓርቲ ወገንተኛ ናቸው ከሳሽን በመሰሉ ተፎካካሪያ የሆኑ ፓርቲዎችን በተመለከተ የሚሰጡት ማስረጃ ሊታመን የሚችል አይደለም የሚል ነው፡፡

ይህ ፍርድ ቤት ይህን ክርክር እንደመረመረው በታችኛው ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላት በሙሉ ለገዢው ፓርቲ ወገንተኛ ይሆናሉ በሚል ግምት በጥቅሉ መውሰድ የሚያስችል ነገር አላገኘም፡፡ በተያዘው ጉዳይም ለገዢው ፓርቲ ወገንተኛ በመሆን የተሰጠ ወይም ሳይሰጥ የቀረ መረጃ ስለመኖሩ የቀረበ ተጨባጭ ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህም ይህን ማስረጃ በሌለበት በመቃወም ክርክር መቅረቡ ተገቢ አይሆንም፡፡

እንዲሁም በምስራቅ ኦሮሚያ ክፍሎች የተደረገው ማጣራት በአስተዳደር አካላት በቂ ጊዜ ተሰጥቶ መረጃ ስላልተሰበሰበ በጥንቃቄና በበቂ ሁኔታ ማስረጃ በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች የማሰባሰብ ግዴታ ተከሳሽ አልተወጣም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ ይህን ክዷል፡፡ ከሳሽ ይህን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡

ፍርድ ቤቱ እንደመረመረው ከላይ እንደተመለከተው በሌሎች አካባቢ መረጃ ተከሳሽ ካሰባሰበበት የወረዳና የቀበሌ ማስረጃ ውጪ ሌላ ስመጠቀሙ ሆነ በተገቢው ላለመከናወኑ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ ባልቀረበበት የተነሳው ክርክር መሆኑ ስለሚታይ አሳማኝነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

በአጠቃላይ ከሳሽ ተከሳሽ ያደረገው የማጣራት ሂደት ግልጽነት መርህን አልተከተለም በሚል ያነሳቸው ክርክሮች ተቀባይነት የላቸውም ተብለዋል፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ

ከሳሽ በክሱ ዋና አድርጎ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተከሳሽ ከፓርቲነት በመሰረዝ የሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ነው፡፡

ከሳሽ በተከሳሽ የተወሰደበትን የመሰረዝ ውሳኔው በመቃወም ያቀረባቸው ዋና ነጥቦች ከላይ እንደተመለከተው ሁለት ሲሆኑ እነርሱም የከሳሽ መከላከል መብቱ ያልተከበረ መሆኑ እና ቦርዱ መስራች አባላት ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችን ያጣራበት ሂደት አግባብነት ያለው አይደለም የሚሉ ቢሆንም ክርክሮቹ ተገቢነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም፡፡

ይህ ከተባለ ተከሳሽ ፓርቲውን በመሰረዝ የሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም የሚባልበት ምክንያት ስለማይኖር የተከሳሽ ውሳኔ እንዲሰረዝ ለማድረግ አይገባም ተብሎ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. ተከሳሽ ከሳሽ ፓርቲ ያቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ እንዲደረግና እንዲሰረዝ የሰጠው ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 65(4) እና 65()()መሰረት ህግን የተከተለ መሆኑ ስለተረጋገጠ ሊሻር አይገባም በማለት ይህ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቷል።

2. ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሳራ ይቻሉ።

3. ይግባኝ መብት ነው። መዝገቡ ተዘግቷል።